ሃላፊነት የጎደለው አስተያየት

ኢብሳ ነመራ

ዶ/ር መረራ ጉዲና የአስቸኳይ ግዜ አዋጁን ተላልፈዋል በሚል ወንጀል ተጠርጥረው በቁጥጥር ስር መዋል የባለፈው ሳምንት የሃገር ውስጥና የውጭ ሚዲያዎች ዜና ሆኖ ሰንብቷል። ዶ/ር መረራ ባለፉት ሁለት አስርት ዓመታት በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲ መሪ በመሆን እንዲሁም በሶስተኛው ዙር ሃገራዊ ምርጫ አሸንፈው የፌደራል የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል ሆነው በማገልገላቸው በማንኛውም ምክንያት በቤተሰብ ጉዳይ ጭምር በህግ በቁጥጥር ስር መዋላቸው ዜና የሆናል። እናም ዜና መሆናቸው በራሱ የሚያስገርም ነገር የለውም። የአስቸኳይ ግዜ አዋጅ ኮማንድ ፖስት በጉዳዩ ላይ በሰጠው መግለጫ ዶ/ር መረራ በቁጥጥር ስር የዋሉት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ማስፈጸሚያ መመሪያ ቁጥር አንድ አንቀጽ 2 ላይ የተመለከተውን መመሪያ ተላልፈው በመገኘታቸው መሆኑን አስታውቋል። የአስሸኳይ ግዜ አዋጅ ማስፈጸሚያ መመሪያ ቁጥር አንድ አንቀጽ 2፤

ከሽብርተኛ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት ማድረግ

- በሽብር ከተሰየሙ ድርጅቶችና ከፀረ ሰላም ቡድኖች ጋር ማናቸውንም ግንኙነት ማድረግ፣
- የአሸባሪ ድርጅቶችን የተለያዩ ጽሑፎች መያዝ ማሰራጨት፣ ዓርማቸውን መያዝ ወይም ማስተዋወቅ፣
- የቴሌቪዥን ወይም የሬድዮ ፕሮግራምን መከታተል፣ የኢሳት፣ የኦ.ኤም.ኤን. እና የመሳሰሉትን የሽብርተኛ ድርጅቶች ሚዲያዎችን ማሳየት፣ መከታተልና ሪፖርት ማድረግ የተከለከለ ነው።

ይላል።

ዶ/ር መረራ በዚህ አንቀጽ መሰረት በቁጥጥር ስር ለመዋል ያበቃቸው በቤልጂየም ብራስልስ የአውሮፓ ህብረት ፓርላማ አባል የሆኑትና የስራ ባለደረቦቻቸውን ጭምር በሚያስገርም ሁኔታ የኢትዮጵያን መንግስት በመቃወም የሚታወቁት ወ/ሮ አና ጎሜዝ በጠሩት ስብሰባ ላይ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሽብርተኝነት ከተፈረጀው ግንቦት 7 መስራችና መሪ ከሆኑት ብርሃኑ ነጋ ጋር ተገናኝተው በኢትዮጵያ ጉዳይ ላይ መምከራቸው ነው። ወ/ሮ አና ጎሜዝ የኢፌዴሪን ህገመንግስታዊ ስርአት ሽብርተኝነትን ጨምሮ በማንኛውም መንገድ አስወግዳለሁ ብሎ ከኤርትራ መንግስት ጋር በመተባበር የሚንቀሳቀሰው ግንቦት 7 የተባለ ቡድን ወዳጅነታቸውም ይታወቃሉ። ግንቦት 7 በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሽብርተኝነት የተፈረጀ ቡድን ነው።

ዶ/ር መረራ በሽብር ከተሰየሙ ድርጅቶችና ከፀረ ሰላም ቡድኖች ጋር ማናቸውንም ግንኙነት ማድረግ የተከለከለ ነው የሚለውን የአስቸኳይ ግዜ አዋጅ ተላልፈዋል በሚል የወንጀል ተጠርጣሪነት በቁጥጥር ስር ለመዋል ያበቃቸው ይህ ነው።

ከዶ/ር መረራ በቁጥጥር ስር መዋል ተከተሎ በተለይ በውጭ ሃጋሪት በሚገኙ ሚዲያዎች የተለያዩ አስተያየቶች ተሰጥተዋል። ከአነዚህ መሃከ ዶ/ር መረራን ቤልጂየም ብራስልስ ለስብሰባ የጠራው አካል የአወሮፓ ህበረት ፓርላማ እነደሆነ አድርገው ያቀረቡ ይገኙበታል። ይህ ፍጹም ስህተት ነው። ዶ/ር መረራን ወደብራስልስ የጠሯቸው የአወሮፓ ህብረት ፓርላማው አባል የሆኑት ወ/ሮ አና ጎሜዝ በግላቸው ናቸው እንጂ ፓርላማው እንደተቋም አይደለም። የአወሮፓ ህብረት ፓርላማ አባላት በፈለጉት ጉዳይ ላይ ሞሽን ለማቅረብ አስቀድመው በግላቸው የፈለጓቸውን አካላት የማነጋገር መብት አላቸው። ይህ ደግሞ የማንኛውም ፓርላማ አባል መብት ነው። ወ/ሮ አና ጎሜዝ በአወሮፓ ህብረት ውስጥ ከወከላቸው የፖርቼጋል ህዝብ በላይ የግንቦት 7 ፍቅርና የኢፌዴሪ መንግስት ጥላቻ እንቅልፍ ሰሊነሳቸው መኖሩ ይታወቃል።

ወ/ሮ አና ጎሜዝ በኢትዮጵያ ጉዳይ ላይ ለመወያየት በሚል የግንቦት 7 መሪዎችንና ሌሎች ጥቂት ግለሰቦችን ጠርተው ሲያወያዩ የሰሞኑ የመጀመሪያቸው አየደለም። ለምሳሌ ባለፈው ዓመት ታህሳስ ወር ገደማ በኢትዮጵያ በተከሰተው ድርቅ ለምግብ እጥረት የተጋለጡ ዜጎች ቁጥር ከ10 ሚሊየን በላይ መድረሳቸው ሲገለጽ በዚህ ጉዳይ ላይ ዶ/ር ብርሃኑንና ሌሎች ጥቂት ወዳጆቻቸውን ጠርተው አንድ ክፍል ውስጥ በጠረጴዛ ዙሪያ አወያይተው እንደነበረ ይታወሳል።

ታዲያ በዚያን ግዜም ይህ ወ/ሮ አና ጎሜዝ የጠሩትን 15 ያህል ሰዎች የተገኙበትን ስብሰባ የአውሮፓ ህብረት ፓርላማ የጠራው በማስመሰል ተዘግቦ ነበር። የአሜሪካ ድምጽ የአማርኛ ፕሮግራም (ቪኦኤ) ሳይቀር ዶ/ር ብርሃኑ ለአውሮፓ ህብረት ፓርላማ በኢትዮጵያ የተከሰተውን ድርቅ አስመልክተው ንግግር አደረጉ በማለት ዘግበውን እንደነበረ ይታወሳል። ይሁን እንጂ የህብረቱ ፓርላማ ይህን እንዳላደረገ ወዲያውኑ ባወጣው መግለጫ አረጋግጦ የአና ጎሜዝ ሸንጎ ወሬ የትም ሳይደርስ ቀርቷል።

አሁንም የሆነው የሄው ነው። ቪኦኤ ግን ይህን ሲዘግብ ዶ/ር መረራ ጉዲና ብራስልስ ለሚገኘው የአወሮፓ ህብረት ፓርላማ ንግግር አደረጉ በሚል ነው። እርግጥ መርሃ ግብሩን ያዘጋጁት ወ/ሮ አና ጎሜዘ መሆናቸውነ አልካደም። የሰሞኑ ዶ/ር መረራና ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ የተገኙበት ሸንጎ በአና ጎሜዝ በግል የተዘጋጀ የውይይተ መድረክ እንጂ የህብረቱ ፓርላማ ስብሰባ አልነበረም። ቪኦኤና መሰል ሚዲያዎች የዚህ አይነት አደናጋሪ ወሬ መነዛት የሚፈልጉበት ምክንያት ለብዎች ግልጽ አይደለም።

ከዚህ ጉዳይ ጋር በተያያዘ ሌላው ሲሰጥ የሰነበተው አስተያየት፣ የብራስልሱ ስብሰባ  በኢፌዴሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በአሸባሪነት የተፈረጀው ግንቦት 7 እና/ወይም መስራችና መሪው ብርሃኑ ነጋ የጠሩት አይደለም፤ እርሳቸውም ተጋበዥ ናቸው በመሆኑም ዶ/ር መረራ በዚህ ጉባኤ ላይ ሲገኙ ከብርሃኑ ነጋ ጋር መገጣጠማቸው ሊያስጠይቃቸው አይገባም የሚል ነው።

ይህን አስተያየት በከፊል ስንመለከተው ትክክል ይመሰላል። ወ/ሮ አና ጎሜዝ በኢፌዴሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በአሸባሪነት ስላልተፈረጁ ዶ/ር መረራ ጉዲና እርሳቸው የጠሩት ስብሰባ ላይ መገኘታቸው በራሱ እንደጥፋት ሊወሰድ አይችልም። ይሁን እንጂ በሽብርተኝነት የተፈረጀው ግንቦት 7 መስራችና መሪ ብርሃኑ ነጋ በዚህ ወዳጃቸው ወ/ሮ አና ጎሜዝ በጠሩት ስብሰባ ስብሰባ ላይ ከሌሎች ታዳሚዎች ጋር ተወያይተው በኢትዮጵያ ጉዳይ ላይ ለመወሰን መገኘታቸውን ሲያውቁ ዶ/ር መረራ በአስቸኳይ ግዜ አዋጁ በሽብር ከተሰየሙ ድርጅቶችና ከፀረ ሰላም ቡድኖች ጋር ማናቸውንም ግንኙነት ማድረግ  የተከለከለ መሆኑን አስታውሰው ራሳቸውን ከወ/ሮ አና ጎሜዝ ስብሰባ ላይ ማግለል ነበረባቸው። ዶ/ር መረራ የግንቦት 7ን ዓላማ የሚደግፉ ቢሆኑ እንኳን፣ በህግ ከመጠየቅ ለመዳን ይህን ማድረግ ብቻ ነው የነበረባቸው። እርግጥ ምክንያታቸውን በይፋ መናገር ይጠበቅባቸው ይሆናል። የህግ የበላይነትን ምንነት የሚያውቁት ዶ/ር መረራ ይህን ያላደረጉት ተሳስተው ሳይሆን የሚያስከተለውን የተጠያቂነት ውጤት እያወቁ ነው። እናም የህግ የበላይነት መከበር ስላለበት፣ እንዲሁም ዶ/ር መረራ ከሌሎች ዜጎች በተለየ ከህግ በላይ የመሆን ምድራዊም ሆነ መለኮታዊ መብትና ስልጣን ስለሌላቸው ለተጠያቂነት በቁጥጥር ስር ውለዋል። ይህ ሁኔታ  አወዛጋቢ ይሆን የነበረው ዶ/ር መረራ በህግ ሳይጠየቁ ቢቀሩ ነበር።

እንግዲህ የህግ የበላይነትን ለማስከበር ዶ/ር መረራ በወነጀል ተጠርጣሪነት በቁጥጥር ስር መዋላቸውን ተከተሎ፣ ማንኛውንም አጋጣሚ ለፖለቲካ ትርፍ መጠቀሚያነት ለማዋል እንዲሁም የኢፌዴሪ መንግስትን ለማሳጣት ዓላማ ለመጠቀም የሚራወጡ ቡድኖችና ግለሰቦች ጉዳዩን ያለወጉ አንሻፈው አስተያየት ሲሰጡ ቆይተዋል፤ አሁንም አለበዘኑም። ይህ የተለመደና የተለየ ትኩረት የሚሰጠው አይደለም። እናም ባሉበት እተዋቸዋለሁ። በተለይ በአሜሪካ የኮንግሬስ አባላት የተሰጡ አስተያየቶችም አሉ። ራሳቸውን የፍርድ ቤት ስልጣን በመስጠተ ዶ/ር መራራ በአስቸኳይ ይፈቱ ያሉ የኮንግሬስ አባላትንም ሰምተናል። የኮንግሬስ አባላቱ የሰጡት አስተያየት የግላቸው ሰለሆነ ብዙመ ዋጋ የሚሰጠው አይደለም።

ይሁን እንጂ በዚህ ጉዳይ ዙሪያ ከተሰጡት አሰተያየቶች መሃከል ምናልባት የአሜሪካ መንግስት አቋምንም እንደሚያንጸባርቅ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል በዬ ያገመተኩት ላይ አስተያየት ልሰጥ ወድጃለሁ። ይህም በአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት ምክትል ቃል አቀባይ ማርክ ቶነር የተሰጠ አስተያየት ነው። ሚ/ር ቶነር ለቪኦኤ በሰጡት አስተያየት . . . ኢትዮጵያ ያወጀችው የአስቸኳይ ግዜ አዋጅ ምናልባት ተቃውሞን ዝም ለማሰኘትና በህገመንግስት የተረጋገጠ የኢትዮጵያውያን መብቶችን ለመንፈግ ጉዳይ እየዋለ ለመሆኑ ያለንን ጥርጣሬ ይበልጥ ያጠናክረዋል። ይህ ሁኔታ የኢትዮጵያ መንግስት የአስቸኳይ ግዜ አዋጁን ባወጣ ግዜ ‘የፖለቲካ ለውጦችን አደርጋለሁ’ ሲል የገባውን ቃል የጻረራል ብለዋል።

ኢትዮጵያ የአስቸኳይ ገዜ አዋጁን ያወጀችው ተቃውሞን ዝም ለማሰኘት ነው የሚለው የሚ/ር ቶነር ጥርጣሬ መሰረተ ቢስ ነው። ሚ/ር ቶነር የአስቸኳይ ግዜ አዋጁ ከመውጣቱ በፊት የነበረውንና የአስቸኳይ ግዜ አዋጁን የግድ ያለውን ሁኔታ አያውቁትም። ወይም በጉዳዩ ላይ ያላቸው መረጃ ውጭ ሃገር ከሚኖሩ ህገመንግስታዊ ስርአቱ በማንኛውም መንገድ መፍረስ አለበት የሚል እምነት ካላቸውና ይህን እነደአቋም ከመያራመዱ ግለሰቦችና ቡደኖች ያገኙት ነው።

በቅድሚያ የአሰቸኳይ ግዜ አዋጁ የታወጀው ሃላፊነትና ተጠያቂነት በሌለው ሁኔታ በማህበራዊ ሚዲያ በተካሄድ ቅስቀሳ በተለያዩ የሃገሪቱ አካባቢዎች ህገመንግስታዊ ስርአቱንና አጠቃላይ ያህገሪቱን ዘላቂ ህልውና ለአደጋ ያጋለጡ፣ ለሰው ህይወት መጥፋትና ለግለሰቦች ለውጭ ኩባንያዎች ጭምር ንብረት መወደምና ለሰዎች ከመኖሪያ መፈናቀል ምክንያት የሆኑ እንዲሁም ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎችን የገቱ ሁከቶች በመነሳታቸው ነው። እነዚህን ሁከቶች በተለመደው ህግና ህግን የማስከበር ስርአት መቆጣጣር አልተቻለም። ይህ ሁሉም ኢትዮጵያውያን የሚመሰክሩት እውነት ነው። እርግጥ አሜሪካ የሚኖሩ አንዳንድ ወገኖች አጋጣሚው ወደስልጣን ሊያወጣን ይችላል የሚል ተሰፋ ስለፈጠረላቸው እነደሚደግፉት ይታወቃል። ባለቤትነቱ የሚ/ር ቶነር መንግስት የሆነው ቪኦኤ የአማርኛ ፕሮግራም ጋዜጠኞችም ሁከቱን የሚያጋግሉና ህዝቡን ውዥንብር ውስጥ የሚከቱ የተዛቡ ዘገባዎችን በማቅረብ ሁከቱን ተስፋ ላደረጉ ወገኖች የነበራቸውን ድጋፍ አሳይተዋል። ከዚህ ውጭ ያሉ በተለይ በሃገር ቤት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ግን፣ ገዢውን ፓርቲ የሚቃወሙ ጭምር የሁከቱ አካሄድ ሃገሪቱን ዳግም ሃገር ልትሆን ባመትችልበት ሁኔታ ሊበታትናትና የአሸባሪዎች መፈንጫ ሊያደርጋት ይችላል የሚል ስጋት አድሮባቸው ነበር። መንግስት ሰላምን ለማስከበር ህጋዊ እርምጃ እንዲወስድም ሲወተውቱ ነበር። የአስቸኳይ ገዜ አዋጁ የታወጀው በዚህ ምክንያት ነው።

ከዚህ በተጨማሪ የአስቸኳይ ግዜ አዋጁ በገዢው ፓርቲ ትእዛዝ በዘፈቀደ የታወጀና የሚመራ ሳይሆን ህገመንግስታዊ ነው። የአስቸኳይ ግዜ አዋጁ በህገመንግስቱ አንቀጽ 93 መሰረት የታወጀና በዚሁ አዋጅ መሰረት የሚፈጸም ነው። መንግስት በአስቸኳይ ግዜ አዋጁ አተገባባር ህገመንግስቱ ከሚፈቅደው ውጭ እንዳችም ነገር ማድረግ አይችልም። እስካሁን ባለው ሁኔታም አላደረገም። እርግጥ ነው የአስቸኳይ ገዜ አዋጁ በሰራ ላይ በሚቆይበት ግዜ የተወሰኑ ፖለቲካዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ሊገደቡ እንደሚችሉ ህገመንግስቱ ያዛል።

የአስቸኳይ ግዜ አዋጅን የሚመለከተው የህገመንግስቱ ድንጋጌ አንቀጽ 93 ንኡስ አንቀጽ 4 ፊደል ተራ ‘ለ’ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ስልጣን በህገ መንግስቱ የተቀመጡትን መሰረታዊ የፖለቲካና ዴሞክራሲ መብቶችን፣ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅን ለማወጅ ምክንያት የሆነውን ጉዳይ ለማስወገድ ተፈላጊ ሆኖ በተገኘው ደረጃ፣ እስከማገድ ሊደርስ የሚችል ነው ይላል። በዚህ መሰረት የአደባባይ ሰልፎችና ስብሰባዎች፣ በተወሰኑ አካባባዎች የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች በሰአት ገደብ የተከለከሉበት ሁኔታ አለ። ይህ ህገመንግስታዊ የሆነ የአስቸኳይ ገዜ አዋጅ ግን በአጠቃላይ ተቃዋሚዎችን ዝም ለማሰኘት ሊውል ይችላል የሚል ጥርጣሬ የሚያስነሳ አይደለም። በተለይ የዶ/ር የመረራ መታሰር ሰላማዊ ተቃውሞን ዝም ከማሰኘት ጋር የሚያገናኘው አንዳችም ተጨባጭ ምክንያት የለም።

ዶ/ር መረራ የተጠረጠሩት መንግስትን ተቃውመው በመናገራቸው አይደለም። መንግስትን በመቃወም ፊት ለፊት የመናገርን ህገመንግስታዊ መብት የዶ/ር መረራን ያህል የተጠቀመ ተቃዋሚ ያለ አይመስለኝም። የአስቸኳይ ገዜ አዋጁ ከታወጀ በኋላ እንኳን በፋና ብሮድካስቲንገ ኮርፖሬት አዘጋጅነት ባሃገሪቱ ወቅታዊ ጉዳይ ላይ የተካሄደ ውይይት ላይ ተጋብዘው መንግስትና ገዢው ፓርቲ ላይ ያላቸውን ተቃውሞ አንዳችም ሳይሰስቱ ተናግረዋል። ይህ ንግግራቸው በሚዲያ ተሰራጭቷል። መንግስት የአስቸኳይ ግዜ አዋጁን ያወጀው የተቃውሞ ድምጾችን ለማፈን ቢሆንማ ኖሮ፣ ቀድሞውኑም በዚህ ውይይት ላይ አይጋብዛቸውም ነበር። ዶ/ር መረራ የተጠረጠሩበት ወንጀለ ቀደም ሲል በጠቀስነው የህግ ድንጋጌ መሰረት በኢትዮጵያ ተቀስቅሶ ከነበረውና ህገመንግስታዊ ስርአቱን ለአደጋ ካጋለጠው ሁከት ጀረባ አለሁበት አያለ ከሚደነፋው፣ በቅርቡ በኤርትራ መንግስት የታጠቁ አሸባሪዎችን በደሃገር ውስጥ ካሰረገው የግንቦተ 7 መሪ ጋር ተገናኘተው በኢትዮጵያ ጉዳይ ላይ ስለመከሩ ነው፤ በቃ።

ሚ/ር ቶነርና መንግስታቸው ለኢትዮጵያ ህዝብ መብት፣ ነጻነት፣ ሰላምና ብልጽግና አሳቢ ከሆኑ ይህን የሚያረጋግጡበት መንገድ የምስራቅ አፍሪካን ቀጠና የማተራመስ ስትራቴጂ ነድፎ ከሚንቀሳቀሰውና አልሸባብን በመሳሪያ ይደግፍ እንደነበረ ተረጋግጦበት በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የጸጥታው ምክር ቤት እስካሁን የጸና ማዕቀብ ከተጣለበት የኤርትራ መንግስት ጋር ግንባር ፈጥሮ ኢትዮጵያን ለማተራመስ የሚራወጠውን፣ አሜሪካ በበጎ አድራጎት ድርጅትነት ተመዝግቦ የተቀመጠውን ግንቦት 7 አደብ እንዲይዝ በማድረግ ብቻ ነው። ይህን ችላ ብለው ስለኢትዮጵያ የሚነዙት ወሬ አብዛኛው ኢትዮጵያዊ ልብ ውስጥ ጠብ የሚል እንዳልሆነ ማወቅ አለባቸው።

ሚ/ር ቶነር፣ መንግስት የአስቸኳይ ገዜ አዋጁን ሲያውጅ የፖለቲካ ማሻሻያ አደርጋለሁ ብሎ ነበር ብለዋል። ዶ/ር መረራን በወንጀል ጠርጥሮ ማሰሩም ይህን እንደሚጻረር ነው የተናገሩት። ይህም ሚ/ር ቶነር ስለአስቸኳይ ግዜ አዋጁ ምንም የማያውቁ መሆኑን ነው የሚያሳየው። መንግስት የአስቸኳይ ግዜ አዋጁን ያወጀው ቀደም ሲል እንደተገለጸው በመደበኛ ህግና ህግን የማስከበር ስርአት መቆጣጠር ያልተቻለ ሁከት በመፈጠሩ በልዩ ህግን የማስከበረ እርምጃ የሃገሪቱን ሰላምና መረጋጋት ወደነበረበት ለመመለስ ነው፤ በቃ። በአስቸኳይ ግዜ አዋጁ ውስጥ አከናውነዋለሁ ያለው የተለየ የፖለቲካ ማሻሻያ የለም።

እርግጥ መንግስት ለሁከቱ መፈጠር ምክንያት ሆነዋል ላላቸው የመልካም አስተዳደር፣ የፍትህ መዛባት፣ የስራ አጥነት ችግር ላይ ለተነሱ የህዝብ ጥያቄዎች፣ እንዲሁም የአመለካከት ብዝሃነትን የበለጠ ማስተናገድ የሚያስችል ስርአት የሚበጅበትን ሁኔታ በስልጣን ዘመኑ ውስጥ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ እንደሚሰራ፣ ከተቻለም በአጭር ግዜ ውጤት ለማምጣት እንደሚጥር ተናግሯል። ይህ ከአስቸኳይ ግዜ አዋጁ ጋር የሚያገናኘው አንዳችም ነገር የለም። ሚ/ር ቶነር መንግስት የአስቸኳይ ግዜ አዋጁ ተግባራዊ በሚሆንባቸው ወራት የፖለቲካ ማሻሻያ አደረጋለሁ ማለቱን የትና ከማን እንደሰሙ እርሳቸው ብቻ ነው የሚያውቁት።

መንግስት የፖለቲካ ማሻሻያ አድርጌያለሁ ብሎ ቢሆን እንኳን የፖለቲካ ማሻሻያ ማድረግ ለተወሰኑ ሰዎች ህግን የመተላለፍ ስልጣን መስጠት ተደርጎ የሚታይበት ምክንያት የለም። እናም የሚ/ር ቶነር አስተያየት መጨበጫ የሌለው ምናልባትም ለማውራት ያህል ያህል ብቻ የተሰጠ መሆኑ አይሎ ይታያል። ይህ ተገቢ አይደለም። ሃላፊነት ላይ ያለ ሰው በሚሰጠው አስተያየት ሃላፊነት ሊሰማው ይገባል።